# የቤት ውስጥ አየርን ማሻሻያ እና የ COVID-19 ስርጭት አደጋን መቀነሻ 3 መንገዶች

ንጹህ የቤት ውስጥ አየር በቤት ውስጥ የ COVID-19 ስርጭትን መቀነሻ አንዱ ውጤታማ መንገድ ነው። የሚከተሉት ዘዴዎች በመቆያዎ ውስጥ ያለውን የውስጥ አየር ለማጽዳት ይረዳሉ:

## 1. የአየር ዝውውርን መጨመር

*የወጪን አየር ወደቤት ውስጥ በታዎች እንዴት ነው ማስገባት የምችለው?*

- ከውጪ ያለ አየር ወደ ህንጻው ውስጥ የሚገባበትን ፍሰት ለመጨመር መስኮቶችን እና በሮችን ይክፈቱ።
- በማሞቂያ፣ አየር ማስገቢያ፣ እና ማቀዝቀዣ (Heating, Ventilation, and Cooling (HVAC)) ስርአቱ በኩል ተስቦ የሚገባውን የውጪ አየር ወደ 100% ይጨምሩ።



## 2. የቤት ውስጥ አየርን ማጽዳት



*በካዮችን እንዴት ነው ከቤት ውስጥ አየር ውስጥ ማስወገድ የምችለው?*

- የ HVAC  ስርአቱን በማሻሻል ወይንም የተንቀሳቃሽ የ HEPA የአየር ማጣሪያዎችን በማድረግ የቤት ውስጥ የአየር ማጣሪያን ይጨምሩ፡
- የ HVAC ስርአቱ የከፍተኛ ውጤታማነት ማጣሪያዎችን (13 ወይም ከዚያ በላይ የ MERV ነጥብ የተሰጣቸው) ማስተናገድ እንደሚችል ያስፈትሹ። ማጣሪያዎችን ከቻሉ ይጨምሩ።
- እስከ 0.3 ቅንጣት ድረስ በ99% ወይም ከዚያ በላይ ውጤታማነት ማጣራት የሚችሉ ተንቀሳቃሽ የ HEPA አየር ማጣሪያዎችን ይጠቀሙ።
- ከጀርባው የ MERV 13 ማጣሪያ ያለው ሳጥንን ይጠቀሙ። ይህ የአነስተኛ ወጪ አማራጭ ነው።

## 3. በአየር ውስጥ ያሉትን ጀርሞች በላይኛው ክፍል የአልትራ-ቫዮሌት ጀርም መግደያ ጨረርን በመጠቀም ጀርሞችን ይግደሉ (UPPER ROOM ULTRAVIOLET GERMICIDAL IRRADIATION (UVGI))

*የ UVGI ስርአቶች በአየር ውስጥ ያሉ ጀርሞችን እንዳይንቀሳቀሱ ማድረግ ይችላሉ፣ ነገር ግን በካዮችን ማስወገድ አይችሉም። UVGI በተወሰኑ ሁኔታዎች ውስጥ የቤት ውስጥ አየርን ዝውውርን እና አየር ማጣራትን ሊያሻሽሉ ይችላሉ።*

- ለቦታዎ የሚመች ከሆነ፣ **የ** UVGI **ስርአቶችን ከባለሙያ ጋር በመሆን ይግጠሙ።**



ለቤትዎ በደምብ የሚሰራልዎትን መንገድ ለመምረጥ **ከህንጻ አስተዳዳሪዎ ጋር ወይም የ HVAC ባለሙያ ጋር ይወያዩ።**

ስለእነዚህ ቴክኖሎጂዎች እና መንገዶች ተጨማሪ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት www.kingcounty.gov/covid/air (ድህረ-ገጹ በእንግሊዘኛ ብቻ ነው ያለው) ይጎብኙ።

April 15,2021

Public Health
Seattle & King County